# Global Storybooks

globalstorybooks.net

## ካላይ ከእጽዋት ጋር ትነጋገራለች

Ursula Nafula
Jesse Pietersen
Mezemir Girma

This work is licensed under a Creative Commons Attribution 4.0 International License.
https://creativecommons.org/licenses/by/4.0

# ካላይ ከእጽዋት ጋር ትነጋገራለች



Ursula Nafula
Jesse Pietersen
Mezemir Girma
2
አማርኛ am



ይቺ ካላይ ነች። ዕድሜዋ 7 ዓመት ነው። የስሟ ትርጉም በቋንቋዋ በሉቡኩሱ ‹‹ጥሩዋ ልጅ›› ማለት ነው።



ካላይ ከእንቅልፏ ስትነሣ ከአንድ የብርቱካን ዛፍ ጋር ትነጋገራለች። ‹‹እባክህ አንተ የብርቱካን ዛፍ ትልቅ ሁንና ብዙ የበሳሰሉ ብርቱካኖችን ስጠን›› ትለዋለች።



ካላይ ወደ ትምህርት ቤት ትሄዳለች። በመንገዷም ላይ ከሳሩ ጋር ታወራለች። ‹‹እባክህ ሳር አረንጓዴነትህን ግፋበት እንጂ እንዳትደርቅ።››





‹‹የብርቱካኑ ፍሬዎች ገና አልበሰሉም›› ካላይ አለች። ‹‹ነገ እመለስና አይሃለሁ የብርቱካን ዛፍ›› አለች ካላይ። ‹‹ምናልባት ያኔ የበሰሉ የብርቱካን ፍሬዎች አዘጋጅተህ ትጠብቀኛ ይሆናል!››



ካላይ ከትምህርት ቤት ወደ ቤቷ ስትመለስ የብርቱካኑን ዛፍ አየችው። ‹‹የብርቱካን ፍሬዎችህ ገና አልበሰሉም?›› ስትል ካላይ ጠየቀችው።





ካላይ የዱር አበቦችን አልፋ ሄደች። ‹‹እባካችሁ አበቦች ለጌጥ ጸጉሬ ላይ እንዳረጋችሁ ማበባችሁን ቀጥሉ።››



በትምህርት ቤት ግቢ ካለው ዛፍ ጋርም ካላይ ትነጋገራለች። ‹‹እባክህ አንተ ዛፍ ከጥላው ስር ቁጭ ብለን እንድናነብ ትላልቅ ቅርንጫፎችን አብቅልልን።››





ካላይ በትምህርት ቤቷ ዙሪያ ካለው ቁጥቋጦም ጋር ታወራለች። ‹‹ጠንካራ ሆናችሁ እደጉ፤ መጥፎ ሰዎች እንዳያልፉ አግዷቸው።››